
# የኢንቨስተሮች ሚና በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ

በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁ.1248/2013 አንቀጽ 2(33) "ኢንቨስተር ማለት ትርፍ ለማግኘት ሲል በዚህ አዋጅ መሰረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የሚገዛ፣ የሚሸጥ ወይም የሚይዝ ማንኛዉም ሰዉ ነዉ" በማለት ይደነግጋል።

ኢንቨስተሮች በካፒታል ገበያ ሥነ ምህዳር ዉስጥ የአንበሳዉን ሚና የሚጫወቱ ሲሆን በተለይ ቶሎ የመሸጥ እና የመግዛት ሁኔታ በመፍጠር በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚደረገውን የካፒታል ፍሰት ሚዛን ያስጠብቃሉ። መንግስት እና ኩባንያዎች የተለያዩ የፋይናንስ አላማቸዉን ለመደገፍ ኢንቨስተሮች በካፒታል ገበያ ከሚያደርጉት ተሳትፎ ገንዘብ በማሰባሰብ ለተለያዩ የፋይናንስ ዓላማዎቻቸዉ ያውላሉ።




## የኢንቨስተሮች ዓይነቶች

የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለሕዝብ ማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 መሠረት ኢንቨስተሮችን የመደበኛ ኢንቨስተሮች፣ ብቁ ኢንቨስተሮች እና የውጪ ኢንቨስተሮች በሚል በሦስት ይከፍላቸዋል።

# መደበኛ ኢንቨስተሮች

መደበኛ ኢንቨስተሮች፡ መደበኛ ኢንቨስተሮች በተቋማዊ ማዕቀፍ ሳይሆን ለግል የኢንቨስትመንት አላማ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የሚገዙ፣ የሚሸጡ ወይም የሚይዙ በግለሰብ ደረጃ የሚሳተፉ ሰዎች ናቸዉ። በቁጥራቸው ብዛት እና የተለያየ የኢንቨስትመንት ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በካፒታል ገበያ የኢንቨስትመንት ዉስጥ ሰፊ ስፍራ የሚይዙ ናቸው። እንዲህ አይነት ኢንቨስተሮች ከብቁ ኢንቨስተሮች ጋር ሲነጻጸሩ ከፍተኛ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል።
የመደበኛ ኢንቨስተሮች ባህሪያት፡-

## የኢንቨስተሮች ዓይነቶች

- መደበኛ ኢንቨስተሮች ከተቋማዊ ኢንቨስተሮች ጋር ሲነፃፀሩ አነስተኛ መጠን ያለው ካፒታል ኢንቨስት የሚያደርጉ ሰሆን፣ ነገር ግን ይህ ኢንቨስትመንት ተጠራቅሞ ከገበያ መጠን አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ድርሻ ይይዛል።
- መደበኛ ኢንቨስተሮች ብዙውን ጊዜ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደለላ ድርጅቶች፣ በበይነ መረብ በሚደረጉ ቀጥታ የኢንቨስትመንት ሥርዓቶች ወይም ከኮሚሽን ነፃ ግብይት በሚያመቻቹ የሞባይል መተግበሪያዎች በኩል ይገበያያሉ። ይህ ተደራሽነትን ቀላል በማድረግ ለአብዛኛው አማካይ አቅም ላላቸው ኢንቨስተሮች ምቹ የኢንቨስትመንት እድሎችን ፈጥሯል።
- መደበኛ ኢንቨስተሮች በአጠቃላይ የካፒታል እድገትን፣ በትርፍ ክፍፍል ወይም በወለድ ክፍያዎች በኩል የገቢ ማመንጨትን ወይም የእነዚህን የሁለቱንም በአንድነት ለማግኘት ያለሙ ናቸው። ልዩ ግቦቻቸው በየግለሰብ የአደጋ ስጋትን በተለይ ኪሳራን መቋቋም እና የፋይናንስ ዓላማዎች ማሳካት ላይ ተመርኩዘው የሚወሰኑ ሲሆን ለጡረታ ቁጠባ፣ ለትምህርት የገንዘብ ድጋፍ ወይም የአጭር ጊዜ የፋይናንስ ግቦችን ለማሳካትን የሚሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ።
- የመደበኛ ኢንቨስተሮች የእውቀት ደረጃዎች በስፋት ሊለያዩ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ልዩ የገበያ እውቀት እና ልምድ የሌላቸዉ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ በምርምር እና በትንተና እየተደገፉ ኢንቨስትመንቶቻቸውን በንቃት የሚያስተዳድሩ ናቸው።
- መደበኛ ኢንቨስተሮች ከተቋማዊ ኢንቨስተሮች ጋር ሲነፃፀሩ ወቅታዊ እና አጠቃላይ የገበያ መረጃ ለማግኘት ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል። ብዙውን ጊዜ ለስሜታዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና በገበያ ሁኔታ ላይ ለሚከሰቱ ለውጦች የበለጠ ተጋላጭ ናቸው፣ ይህም ወደ ምክንያታዊ ያልሆነ የኢንቨስትመንት ምርጫዎች ወይም ውሳኔዎች ሊወስዳቸው ይችላል።

# ብቁ ኢንቨስተሮች

ሁለተኛው ዓይነት ኢንቨስተሮች ብቃት ያላቸዉ ኢንቨስተሮች ሲሆኑ ፣ ይህም ከፍተኛ የተጣራ ሀብት ያላቸው ግለሰቦችን ማለትም መደበኛ አንድ ቤት እና የቤት መኪና ሳይጨምር ከአስር ሚሊዮን ብር በላይ የተጣራ ሀብት ያላቸውን እና ተቋማዊ ኢንቨስተሮችን ያጠቃልላል። ይህም የጡረታ ፈንድ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ባንኮች፣ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት፣ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶችን እና በመንግስት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን ያካትታል።

የተቋማዊ ኢንቨስተሮች በደንበኞች ወይም በአባላት ስም ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስተዳድሩ ናቸው። እነዚህ አካላት ብቁ ኢንቨስተሮች እንደመሆናቸው መጠን በፋይናንስ ገበያዎች ከፍተኛ ካፒታል፣ እውቀት እና ተጽዕኖ የሚያመጡ ናቸው። የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎቻቸው ለገበያው መረጋጋትን፣ ግልጽነትን እና ከጠቅላላው የኢኮኖሚ ግቦች ጋር የተጣጣሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። የተቋማዊ ኢንቨስተሮች ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

የጡረታ ፈንድ፡ የጡረታ ፈንድ በአሠሪዎች፣ በማህበራት ወይም በመንግሥት አካላት የተቋቋሙ የኢንቨስትመንት ፈንድ ሲሆኑ ለሠራተኞች የጡረታ ገቢ ይሰጣሉ። የጡረታ ፈንዶች ሠራተኞች በስራ ዘመናቸው ላይ በሚሆኑበት ጊዜ መዋጮ ይሰበስባሉ፣ የተሰበሰበውን ገንዘብ ትርፍ ለማግኘት በተለያዩ ንብረቶች ላይ ኢንቨስት ያደርጋሉ። የጡረታ ፈንድ ከፍተኛ ሀብት ካላቸው ዋና ዋና የተቋማዊ ኢንቨስተሮች አንዱ ሲሆን በካፒታል ድልድል ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል።

ሁለቱ የኢትዮጵያ የጡረታ ፈንዶች፣ የመንግሥት ሠራተኞች የማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር እና የግል ድርጅት ሠራተኞች የማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የካፒታል ገበያ ልማት ቁልፍ አንቀሳቃሾች የመሆን አቅም አላቸው። የጡረታ ፈንዶች እንደ ቦንድ፣ አክሲዮን፣ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ያሉ የመንግስት እና የግል ኩባንያዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት ያደርጋሉ። የጡረታ ፈንዶች በስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንቶቻቸው የኢኮኖሚ እድገትን፣ መሠረተ ልማትን እና የኢንተርፕራይዝ እድገትን ፋይናንስ የሚያደርጉ ናቸው። የጡረታ ፈንዶች ንቁ ተሳትፎ በካፒታል ገበያው ቶሎ የመሸጥ እና የመግዛት ሁኔታ እንዲስፋፋ፣ የፋይናንስ ገበያዎች ጥልቀት እንዲኖራቸው ብሎም ፋይዳው የጎላ የካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር ለመገንባት አስተዋጽኦ ያደርጋል። የጡረታ ፈንድ ኃላፊነት በሚሰማው እና ስልታዊ በሆነ መልኩ ኢንቨስት የሚደረግ ከሆነ የሃገራችንን የኢኮኖሚ እድገት በመደገፍ የአሁን እና የወደፊት ጡረተኞችን ጥቅም ሊያስጠብቅ ይችላል።

የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፡ የኢንሹራንስ(መድን) ኩባንያዎች ለተወሰኑ አደጋዎች (ሕይወት፣ ጤና፣ ንብረት) መድን ሽፋን ለመስጠት ከፖሊሲ ባለቤቶች አረቦን ይሰበስባሉ። ኢንሹራንሶቹ የተሰበሰቡትን አረቦኖች ትርፍ ለማመንጨት እና የወደፊት የኢንሹራንስ ጥያቄዎችን መክፈል መቻላቸውን ለማረጋገጥ ኢንቨስት ያደርጋሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የመንግስት እና የግል የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በአገሪቱ ውስጥ ቁልፍ የፋይናንስ ዘርፍ ተዋናዮች ሲሆኑ ለግለሰቦች እና ለንግድ ድርጅቶች የአደጋ ስጋት አስተዳደር ሽፋን በመስጠት እናየፋይናንስመረጋጋትን በማስፈን ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።የኢንሹራንስኩባንያዎችለካፒታል ገበያ ልማት አስተዋጽኦ የማድረግ ከፍተኛ አቅም አላቸው። የኢንሹራንሶች ፖርትፎሊዮቻቸው ከፖሊሲ ባለቤቶች የሚሰበሰቡትን አረቦኖች በመጠቀም በመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ በኮርፖሬት ቦንዶች፣ በአክሲዮኖች፣ በጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች እና በሌሎች የፋይናንስ መሳሪያዎች ላይ ኢንቨስት ማድረግን ያካትታል።

# ባንኮች፡

ባንኮች፡ ባንኮች ተቀማጭ ገንዘብ የሚቀበሉ፣ ብድር የሚያቀርቡ እና የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የፋይናንስ ተቋማት ናቸው። እንዲሁም የራሳቸውን ገንዘብ እና የደንበኛ ንብረቶችን በማስተዳደር በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋሉ። ብቁ ኢንቨስተሮች እንደመሆናቸው መጠን ብዙውን ጊዜ በትላልቅ እና በተራቀቁ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እና ግብይቶች ውስጥ ይሳተፋሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ባንኮች የአገሪቱ የፋይናንስ ሥርዓት መሠረታዊ ምሰሶዎች ሲሆኑ ለገንዘብ ግብይቶች፣ ለብድር አቅርቦት እና ለኢኮኖሚ ዕድገት ዋነኛ መንገድ ሆነው ያገለግላሉ። እነዚህ ባንኮች በደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ በኩል ከፍተኛ መጠን ያለው የፋይናንስ ሀብት ይይዛሉ፣ ይህም የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለመደገፍ ሊንቀሳቀስ ይችላል። በተለይ በካፒታል ገበያ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ በተመለከተ ባንኮች ገንዘባቸውን በመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ በኮርፖሬት ቦንዶች፣ በአክሲዮኖች፣ እና በጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች ኢንቨስት ሊያደርጉ ይችላሉ።

በተጨማሪም ባንኮች አክሲዮኖችን እና ቦንዶችን በማውጣት እና በመሸጥ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግብይት በመደገፍ የካፒታል ገበያውን እድገት ያፋጥናሉ፣ በዚህም ለመደበኛ እና ለተቋማዊ ኢንቨስተሮች አማራጭ የኢንቨስትመንት እድሎችን ይከፍታሉ። ለባንኮች በብድር ግምገማ እና በአደጋ ስጋት አስተዳደር ላይ ያላቸው ከፍተኛ እውቀት እና ልምድ በገበያ ውስጥ ያሉትን የፋይናንስ ሰነድ አይነቶች አጠቃላይ የጥራት ደረጃ እና የገበያ መረጋጋት ሊያሻሽል የሚችል ነው።

ባንኮች ለኢኮኖሚ ፕሮጀክቶች ፋይናንስ በማቅረብ እና የመንግስት መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን በመደገፍ በካፒታል ገበያ ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ። የእነሱ ስትራቴጂካዊ ተሳትፎ ኢኮኖሚያዊ አቅምን ለማሳደግ፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ብሎም ለኢትዮጵያ ሰፊ የኢኮኖሚ እድገት እና የልማት ግቦች ለማሳካት አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የፌዴራል እና የክልል መንግስታት፡ በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አካላት በሃገር ውስጥ እና በውጪ የእዳ ሰነዶችን ማውጣት እና መሸጥ ይችላሉ። የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የካፒታል ገበያን ልማት ጨምሮ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ገጽታ በመቅረጽ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። የእነሱ ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ ለኢንቨስትመንት፣ ለፋይናንስ መረጋጋት እና ለኢኮኖሚ እድገት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር አስፈላጊ እና ወሳኝ ነው።

የፌዴራል መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ገቢውን ወይም ትርፍ ገንዘቡን በረጅም ጊዜ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት በማድረግ በካፒታል ገበያ ውስጥ እንደ ወሳኝ ኢንቨስተር ሆኖ ያገለግላል። የፌዴራል መንግስት የኢንቨስትመንት ክንፍ በሆነው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በኩል ስትራቴጂክ እቅዶቹን ለማሳካት ገንዘቡን በካፒታል ገበያ ውስጥ እንደ ስትራቴጂካዊ ኢንቨስተር ሆኖ በመንግስት ሰነዶች፣ የኮርፖሬት ቦንዶች እና ሰነዶች ላይ ኢንቨስት በማድረግ የሀገር አቀፍ የልማት ግቦችን ለመደገፍ፣ የኢኮኖሚ እድገትን ለማሳለጥ እና የግል ዘርፍ ተሳትፎን ለማሳደግ ሊሳተፍ ይችላል።

በተጨማሪም ሆልዲንጉ ገቢ ለማመንጨት፣ የአደጋ ስጋቶችን ለማስተዳደር እና የአገሪቱን የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋት ለማዳበር ኢንቨስት እንደሚያደርግ ይጠበቃል። ከሁሉም በላይ ሆልዲንጉ በካፒታል ገበያ ቶሎ የመሸጥ እና የመግዛት ሁኔታ እንዲፈጠር በማድረግ እና በሌሎችም የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ኢንቨስት በማድረግ ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አጠቃላይ እድገት በንቃት አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የክልል መንግስታት የልማት ስራዎቻቸውን በገንዘብ ለመደገፍ የብድር ሰነድ/ቦንድ/ በማውጣት እና በመሸጥ የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ ከመደበኛ እና ከተቋማዊ ኢንቨስተሮች መሰብሰብ ይችላሉ።

# የመንግስት የልማት ድርጅቶች፡

የመንግስት የልማት ድርጅቶች፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የመንግስት ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ድርጅቶች ሲሆኑ እንደ ኢነርጂ፣ ማዕድን፣ ትራንስፖርት አገልግሎቶች ባሉ ቁልፍ ዘርፎች ውስጥ የተሰማሩ ናቸው። የልማት ድርጅቶቹ ትርፍ ገቢዎችን ወይም ትርፍን በፕሮጀክቶች ወይም በፋይናንስ ገበያዎች ላይ ኢንቨስት ያደርጋሉ። እነዚህ ድርጅቶች አብዛኛውን ጊዜ በኢንቨስትመንት ውስጥ የሚሳተፉት የመንግስትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ አላማዎች ለመደገፍ እና ለማስፈጸም ነው።

ለአብነትም እንደ ኢትዮ ቴሌኮም እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአገሪቱ የካፒታል ገበያ ውስጥ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተቋማዊ ኢንቨስተሮች ሆነው የማገልገል ከፍተኛ አቅም ያላቸው ናቸው። ድርጅቶቹ ገቢያቸውን ወይም ትርፋቸውን በተለያዩ ፕሮጀክቶች ወይም የገንዘብ ሰነዶች ላይ በማዋል የካፒታል ገበያን በጥልቀት እና በስፋት ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ድርጅቶቹ በስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንቶቻቸው አስፈላጊ የሆነ ቶሎ የመሸጥ እና የመግዛት ሁኔታ መፍጠር፣ የገበያ ሁኔታዎችን ማረጋጋት እና በግል ኢንቨስተሮች መካከል በራስ መተማመንን እንዲዳብር ያደርጋሉ። ከዚህም በላይ የእነሱ ተሳትፎ ከብሔራዊ የኢኮኖሚ ግቦች ጋር የሚጣጣሙ ትላልቅ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን፣ የኢንዱስትሪ ልማትን እና የቴክኖሎጂ ፈጠራን ፋይናንስ ማመቻቸት ይችላል። እንደ ተቋማዊ ኢንቨስተሮች ድርጅቶቹ የካፒታል ገበያዎችን እድገት መደገፍ እና ለዘላቂ ልማት የሀገር ውስጥ ቁጠባን ማሰባሰብ፣ በመጨረሻም የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ አቅምን ማጠናከር እና የረጅም ጊዜ የፋይናንስ መረጋጋትን ማሳደግ ያሳድጋሉ።

# የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች፡

የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች፡ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች ከብዙ ኢንቨስተሮች ገንዘብ በማሰባሰብ በባለሙያ የገንዘብ አስተዳዳሪዎች በሚተዳደሩ የተለያዩ የፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንቶች ላይ ኢንቨስት ያደርጋሉ።

የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች የሚከተሉትን ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው። እነዚህ ፈንዶች በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ውስጥ ልክ እንደ ተቋማዊ ኢንቨስተሮች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ፈንዶቹ ከመደበኛ እና ተቋማዊ ኢንቨስተሮች ገንዘብ በማሰባሰብ የተለያዩ የሀብት አይነቶች ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉ ናቸው። በዚህም የኢንቨስትመንት አደጋን በመቀነስ ትርፍን ያሳድጋሉ።

የዚህ ፈንድ ኢንቨስትመንት አሰራር ዝቅተኛ ኢኮኖሚ ላይ ለሚገኙ ኢንቨስተሮች ተደራሽ ያልሆኑ ትላልቅ የኢንቨስትመንት እድሎችን በየደረጃው ሁሉም እንደየአቅሙ ኢንቨስት እንዲያደርግ በማስቻል የካፒታል ገበያን አካታችነት የሚያረጋግጥ ነው። በተጨማሪም የጋራ የኢንቨስትመንት መርሃ ግብሮች በካፒታል ገበያ ቶሎ የመግዛት እና የመሸጥ ሁኔታ እንዲኖር በማድረግ፣ በፈንድ አስተዳደር ውስጥ ምርጥ ልምዶች እንዲበረታቱ በማድረግ፣ የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ኢንቨስተሮችን በመሳብ በኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ፣ ሁሉን አቀፍ እና ተለዋዋጭ የካፒታል ገበያ እንዲኖር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

የውጪ ኢንቨስተሮች፡- ሦስተኛው ዓይነት ኢንቨስተሮች የውጪ ኢንቨስተሮች ሲሆኑ የውጪ ዜጎችን፣ የውጪ ባለቤትነት ያላቸው ድርጅቶችን እና በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሆኖ የውጪ ኢንቨስተርነት ደረጃን የሚመርጡ እና በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያዎች የሚሳተፉ የውጪ ኢንቨስተሮችን ያካትታሉ። የውጪ ኢንቨስተሮች የኢኮኖሚ እድገትን፣ የቴክኖሎጂ እድገትን እና በዓለም አቀፍ ገበያዎች ጋር ትስስርን በማሳደግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

# የኢንቨስተሮች ጥበቃ ማዕቀፍ

የኢንቨስተር መብቶች እና ጥበቃዎች፡- ኢንቨስተሮች በካፒታል ገበያ መሰረታዊ መብታቸው የሆኑትን የደንበኛ ሳቢ መግለጫን ጨምሮ የግብይት ማረጋገጫዎችን እና ስለሂሳባቸው የሩብ ዓመት መግለጫዎችን የማግኘት፣ ድምጽ የመስጠት መብቶች፣ ከኢኮኖሚ መብቶች በተለይ የትርፍ ክፍፍል ክፍያዎች እና ቅድሚያ የመግዛት መብቶች፣ ከካፒታል ገበያ ተዋናዮች ጋር ለሚኖራቸው አለመግባባት ቅሬታቸው በአፋጣኝ መልስ የሚያገኙበት ሥርዓቶች፣ ካሳ የማግኘት መብት፣ የባለሥልጣኑ የቅሬታ መቀበያ ፖርታል እና በመጨረሻም ይግባኝ ለካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት የማቅረብን ጨምሮ ሌሎች መብቶችም አሏቸው።

የክርክር አፈታት እና ካሳ፡- ኢንቨስተሮች ቅሬታቸውን ለገበያው ወይም ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ለተገበያይ አባላት ጥፋቶች በደንበኞች የካሳ ፈንድ በኩል ካሳ መጠየቅ ይችላሉ። በኢንቨስተሮች እና በተገበያይ አባላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በገበያው በተቀናጀ የግልግል ዳኝነት ወይም ሽምግልና ሊፈቱ ይችላሉ። በመጨረሻም ባለሥልጣኑ ወይም እንደ ገበያው ያሉ ራሳቸውን በራሳቸው በሚቆጣጠሩ ድርጅቶች በሚሰጧቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኙ ኢንቨስተሮች ይግባኛቸውን ለካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት አላቸው።